የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፵፬
አዲስ አበባ – ሰኔ ፭ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4[th] Year No. 44
ADDIS ABABA - 12[th] June, 1998

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፴፮/፲፱፻፺ ዓ.ም.
የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ ........ ገጽ ፯፻፶፰

## CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 36/1998
Investment Incentives Council of Ministers (Amendment) Regulations ........ Page 758

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፴፮/፲፱፻፺
### የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብን ለማሻሻል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፴፯/፲፱፻፹፰ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፱ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት (ማሻሻያ) ደንብ ቁጥር ፴፮/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· <u>ማሻሻያ</u>

የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፯/፲፱፻፹፰ እንደሚከተለው ተሻሽሏል ፤

፩· የደንቡ አንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተራ ፊደል (ሀ) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ተራ ፊደል (ሀ) ተተክቷል፤

ሀ) ካፒታሉ እስከ ብር ፪ሚሊዮን ሲሆን … ፵፭%፤ ሆኖም ለማስፋፊያ ወይም ለማሻሻያ ፕሮጀክቱ የተመደበው የኢንቨስትመንት ካፒታል የድርጅቱን ጠቅላላ የኢንቨስትመንት ካፒታል ቢያንስ ወደ ብር ፪፻፶ሺህ ከፍ ማድረግ አለበት ፤"

፪· የደንቡ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፬) ፣ (፭) እና (፮) ተሠርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) እና (፭) ተተክተዋል ፤

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS No. 36/1998
### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO AMEND THE INVESTMENT INCENTIVES REGULATIONS

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 9 of the Investment Proclamation No. 37/1996 (as amended).

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Investment Incentives Council of Ministers (Amendment) Regulations No. 36/1998."

2. *Amendment*

The Investment Incentives Council of Ministers Regulations No. 7/1996 are amended as follows:

1. Sub-Article 2 (a) of Article 6 of the Regulations is hereby deleted and replaced by the following new sub-Article 2 (a):

(a) Where the capital is up to Birr 2,000,000 ... 45%; However, the capital allocated for the expansion or upgrading of the project should increase the total capital of the company to at least Birr 250,000.

2. Sub-Articles 4, 5 and 6 of Article 11 of the Regulations are deleted and replaced by the following new sub-Articles 4 and 5:

"፬· ማናቸውም የካፒታል ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ይፈቀዳል ፡፡ ሆኖም ከውጭ የሚገቡትን ሊተኩ የሚችሉ የካፒታል ዕቃዎችና መሣሪያዎች በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ከሆነ ከውጭ የሚገቡት ከቀረጥ ነፃ ሆነው እንዳይገቡ ቦርዱ በየጊዜው በሚያወጣው መመሪያ ሊያግድ ይችላል ፡፡

፭· ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆኖ የገባ ማናቸውም ዕቃ ሊከፈልበት ይገባ የነበረው የጉምሩክ ቀረጥ አስቀድሞ ሳይከፈልበት የቀረጥ ነፃ መብት ለሌለው ሰው ሊተላለፍ አይችልም፡፡"

፫· ከደንቡ አንቀጽ ፳፪ በኋላ የሚከተሉት አዲስ አንቀጾች ፳፫፣ ፳፬፣ ፳፭፣ ፳፮ እና ፳፯ ተጨምረዋል ፤

"፳፫· ለመከላከያ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት የሚፈቀዱ መሣሪያዎች

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፫ (እንደተሻሻለ) የተደነገገው ለመከላከያ ኢንዱስትሪም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፳፬· ለኢንዱስትሪ መንደር ኢንቨስትመንት የሚፈቀዱ መሣሪያዎች

ለኢንዱስትሪ መንደር የሚያስፈልጉ መሣሪያ ዎችና ዕቃዎች እንዲሁም በቀጥታ ለኢንዱ ስትሪ መንደር ሕንፃ ግንባታ የሚያገለግሉ በሀገር ውስጥ የማይመረቱ መሣሪያዎችና ማቴሪ ያሎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ይፈቀዳል፡፡

፳፭· ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ኢንቨስትመንት የሚፈቀዱ መሣሪያዎች

ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት የሚያስፈልጉ ቋሚ መሣሪያዎችና ዕቃዎች በዋጋ ከ፲፭% ከማይበልጥ የመለዋወጫ ዕቃዎቻቸው ጋር ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ይፈቀዳል፡፡

፳፮· ለምርምርና ስርፀት ኢንቨስትመንት የሚፈቀዱ መሣሪያዎች

ለምርምርና ስርፀት ኢንቨስትመንት የሚያስ ፈልጉ ቋሚ ዕቃዎችና መሣሪያዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ይፈቀዳል፡፡

፳፯· ለካፒታል ዕቃዎች ኪራይ አገልግሎት የሚፈቀዱ መሣሪያዎች

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፫፣ ፲፰ – ፳፪ የተመለከ ቱትን እንዲሁም ለማዕድንና ለፔትሮሊየም ሥራዎች እንደ ካፒታል ዕቃ የሚያገለግሉ መሣሪያዎችን ለኪራይ አገልግሎት ለማዋል ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ይፈቀዳል፡፡"

፬· የደንቡ አንቀጽ ፳፫፣ ፳፬ እና ፳፭ እንደ ቅደም ተከተ ላቸው አንቀጽ ፳፰፣ ፳፱ እና ፴ ሆነዋል፡፡

፭· በደንቡ ሠንጠረዥ አንድ ተራ ፊደል "መ" ሥር የሚከተሉት አዲስ ተራ ቁጥር ፶ እና ፶፩ ተጨምረዋል ፤

"፶· የመከላከያ ኢንዱስትሪ (2927)፤

፶፩· የኢንዱስትሪ መንደር (7010)፡፡"

፮· በደንቡ ሠንጠረዥ አንድ ሥር የሚከተሉት አዲስ ተራ ፊደል "ረ"፣ "ሰ"፣ "ሸ"፣ እና "ቀ" ተጨምረዋል፤

"ረ) የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት (6420)፤

ሰ) ምርምርና ስርፀት (7310 ፡ 7320)፡፡"

"4. Capital goods shall be imported free of customs duty; provided, however, where substitutes of capital goods to be so imported are locally produced, the Board may by directives to be issued from time to time prohibit the importation of such capital goods.

5. Goods imported free of customs duty shall not be transferred to third parties not entitled to duty-free privileges, unless prior payment of customs duty is effected thereon."

3. The following new Articles 23, 24, 25, 26 and 27, are added after Article 22 of the Regulations:

"23. *Equipment to be Imported Duty Free for Defence Industries*

The Provisions of Article 13 of these Regulations (as amended) shall apply to investment in defence industries.

24. Equipment to be Imported Duty Free for Setting up Industrial Estates

Machinery and equipment necessary for setting up industrial estates as well as equipment and materials to be used directly for the construction of industrial estates and not locally produced shall be allowed to be imported free of customs duty.

25. *Equipment to be Imported Duty Free for Telecommunication Services*

Machinery and equipment of durable nature together with spare parts of up to 15% of their value necessary for telecommunication services shall be exempt from payment of customs duty.

26. *Equipment to be Imported Duty Free for Research and Development Purposes*

Machinery and equipment of durable nature necessary for research and development investment purposes shall be exempt from payment of customs duty.

27. *Equipment and Machinery to be Imported Duty Free for Investment in Leasing of Capital Goods*

With respect to activities enumerated under Articles 13, 18-22 of these Regulations as well as to mining and petroleum operations, machinery and equipment necessary to be used for leasing of capital goods shall be exempt from payment of customs duty."

4. Articles 23, 24 and 25 of the Regulations are renumbered as Article 28, 29 and 30, respectively.

5. The following new items No. 50 and 51 are added under Schedule One "D" of the Regulations:

"50. Defence Industries (2927);

51. Industrial estates (7010)."

6. The following new headings "F", "G", "H" and "I" are added under Shedule One of the Regulations:

"F. Telecommunication services (6420);

G. Research and Development (7310, 7320);

ሸ) <u>ትምህርት</u>

፩. ጠቅላላ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት (80210)

፪. የሁለተኛ ደረጃ የቴክኒክና የሙያ ትምህርት (80220 ፣ 80901)

፫. ከፍተኛ ትምህርት (80300)

ቀ) <u>ጤና</u>

፩. ሆስፒታሎች (85110) (ከአዲስ አበባ ውጭ ሲሆን)

፪. የዲያግኖስቲክስ ምርመራ ማዕከሎች (85190) (ከአዲስ አበባ ውጭ ሲሆን)"

፯. የደንቡ ሠንጠረዥ ሁለት ተራ ፊደል "ረ" ተራ ቁጥር ፫፣ ፬ እና ፭ ተሠርዘዋል።

፰. የደንቡ ሠንጠረዥ ሁለት ተራ ፊደል "ሰ" ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ተራ ፊደል "ሰ" ተተክቷል ፤

"ሰ) <u>ጤና</u>

፩. ሆስፒታሎች (85110) (በአዲስ አበባ ውስጥ ሲሆን)

፪. የጤና ጣቢያዎች (85120)

፫. የዲያግኖስቲክ የምርመራ ማዕከሎች (85190) (በአዲስ አበባ ውስጥ ሲሆን)

፬. ክሊኒኮች (85120)"

፱. በደንቡ ሠንጠረዥ ሦስት ሥር የሚከተለው አዲስ ተራ ፊደል "ሰ" ተጨምሯል ፤

"ሰ) የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት (7112 ፣ 7113 ፣ 7129)።"

፫. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፭ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር



H. *Education*

1. General Secondary Level Education (80210)
2. Technical and Vocational Secondary Education (80220, 80901)
3. Higher Education (80300);

I. *Health*

1. Hospitals (85110) (outside Addis Ababa only)
2. Diagnostic Centers (85190) (outside Addis Ababa only)."

7. Under the heading "F" of Schedule Two of the Regulations items 3, 4 and 5 are deleted.
8. The heading "G" of Schedule Two is hereby deleted and replaced by the following new heading "G":

"G. *Health*

1. Hospitals (85110) (within Addis Ababa)
2. Health Centers (85120)
3. Diagnostic Centers (85190) (within Addis Ababa only).
4. Clinics (85120)"

9. The following new heading "G" is added under Schedule Three of the Regulations:

"G. Leasing of Capital Goods (7112, 7113, 7129)."

3. *Effective Date*

These Regulations shall enter into force as of the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 12th day of June, 1998.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA